# አማርኛ ቋንቋ ትምህርት

# አሥራ ሁለተኛ ክፍል

# *የመጀመሪያው ወሰነ-ትምህርት*

**ምዕራፍ:- አንድ፤ ቋንቋና ህብረተሰብ** (*ክፍለ ጊዜ 12*)

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት:-*** *ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ:- የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ከነቤተሰቦቻቸው ይገልፃሉ፣ ያንዳንዱ ቋንቋ ለብሔር ብሔረሰቡ ያለውን ፋይዳ ይናገራሉ፤ ይጽፋሉ፤ ቃላትን በድምፀ-ልሣናዊ ዘዴ ይተነትናሉ፤ በቀለማዊ አጻጻፍ ዘዴም ይጽፋሉ፤ ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ይሰጣሉ፤ ዋቢ መፃሕፍትን ይጠቀማሉ፤ በጽሑፍ አዘጋጅተው ያብላሉትን ሃሣብ ዋና ዋና ነጥብ ይናገራሉ፤ አጫጭር ዓ/ነገሮችንና አንቀጾችን ይተረጉማሉ፤ ምሳሌአዊ አነጋገር የሚገኝበት ዐውድ በመፍጠር አጭር ጽሑፍ ይጽፋሉ::*

| *የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ* | *ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/* | *የክሂሎት ብቃት* | *የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ* |
|---|---|---|---|
| *ቋንቋና ህብረተሰብ* | • *የኢትዮጵያ ቋንቋዎች*<br>• *ቀለማዊ አጻጻፍ ዘዴ*<br>• *ድምፀ-ልሣናዊ አፃፃፍ ዘዴ*<br>• *ለቃላት ቀጥተኛ /መዝገበ-ቃላዊ/ ፍች*<br>• *ከመገናኛ ብዙሃን በመቅረጸ-ድምፅ ከተቀረፀ ናሙና የምርምር ውጤቶችን ማዳመጥ*<br>• *በጽሑፍ ከተዘጋጀ በኋላ ሃሣቡን አብላልቶ ዋና ዋና ነጥቦችን በንግግር ማቅረብ*<br>• *ከመጻሕፍት ሃሣብ ማግኘት*<br>• *ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጐም*<br>• *ምሳሌአዊ አነጋገር* | • *ስለቋንቋ ምንነት፣ አገልግሎትና መሠረ ዊ ጠባዮቹ ካላቸው ግንዛቤ አንፃር አንዳንድ ነጥቦችን መናገር*<br>• *የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ከነቤተሰቦቻቸው ዘርዝሮ መናገር*<br>• *አንድ ቃል በውስጡ የያዛቸውን ድምጾች ተናባቢና አናባቢውን አከ ትሎ ጽፎ ማቅረብ*<br>*ምሳሌ:- መከረ ምኧ-ክክኧ-ርኧ*<br>*ጉትቻ ግኡ-ት -ችኣ*<br>• *ቃሉ የተፈጠረባቸው ተናባቢና አናባቢ ድምጾችን ያቀናጁ ቀለም መመሥረት*<br>*ምሳሌ:- መከረ ምኧ-ክክኧ-ርኧ*<br>*ጉትቻ ግኡ-ት -ችኣ*<br>• *መዝገበ ቃልን በመጠቀም ለቃላት ፍች መስጠት*<br>• *ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች በተካሄደ ጥናትና ምርምር የተገኙ ውጤቶችን ከመቅረጸ-የሚተላለፈውን አዳምጠው ፍሬ ሃሣብ መውሰድ* | • *10ኛ ክፍል የተማሩትን በማስ ወስ ስለቋንቋ ምንነት፣ አገልግሎትና መሠረ ዊ ጠባዮች ካላቸው ግንዛቤ አንፃር ንዲገልጹ ማድረግ*<br>• *የኢትዮጵያ ቋንቋዎችንና ቤተሰቦቻቸውን በዋቢ መጻሕፍት በመ ገዝ ዘርዝረው ንዲያቀርቡ ማበረ ት*<br>• *አንድ ቃል በውስጡ የያዛቸውን ድምጾች /ተናባቢና አናባቢ/ አከ ትለው ንዲጽፉ በምሳሌ አሳይቶ መልመጃ ማሠራት*<br>• *አንድ ቃል የተፈጠረባቸውን ተናባቢና አናባቢ ድምጾች ያቀናጁ፣ ቀለም የሚሆኑትን የለዩ ንዲያሳዩ ምሳሌ አሳይቶ መልመጃ ማሠራት*<br>• *ከምንባቡ ውጭና ውስጥ ለቀረቡ ቃላት ቀጥተኛ /መዝገበ-ቃላዊ/ ፍቺ ንዲሰጡ ማድረግ*<br>• *ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች የተደረገን የጥናትና ምርምር ውጤት ከመገናኛ ብዙ ን አዳምጠው የሰበሰቡትን ሃሣብ ክፍል ውስጥ ማስነበብ*<br>• *የ ያንዳንዱ ብሔረሰብ ቋንቋ ለየብሐረሰቡ ስለሚሰጠው ጠቀሜ ጽሑፍ በማዘጋጀትና ሃሣቡን በማብላላት ዋና ዋና ነጥቦችን በመጠቀም ንግግር ንዲያቀርቡ ማገዝ*<br>• *አጫጭር ዓ/ነገሮችንና አንቀጾችን ሰጥቶ ትምህርት ወደሚሰጥባቸው ሃገራዊ ቋንቋዎች፣ ካላመቸም ወደ ንግሊዝኛ ቋንቋ ንዲተረጉሙ ማበረ ት*<br>• *ምሳሌአዊ አነጋገሮችን ሰጥቶ በመረጡትና ምሳሌአዊ አነጋገሩ ሊገኝበት በሚችል አውድ አጭር ጽሑፍ ንዲጽፉና ንዲያነቡ ማድረግ* |

| የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ | ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/ | የክሂሎት ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ |
|---|---|---|---|
| | | ድምፅና ከመገናኛ ብዙሃን<br>• ያንዳንዱ ብሔረሰብ በራሱ ቋንቋ ቁሳዊና ሕሊናዊ ባህሉን መግለጹና መሠረ ዊ ትምህርት መስጫ ሆኖ ማገልገሉ የሚሰጠውን ጠቀሜ በጽሑፍ በማዘጋጀትና ሃሣቡን በማብላላት ዋና ዋና ነጥቦችን በንግግር ማቅረብ<br>• የኢትዮጵያ ቋንቋዎችንና ቤተሰቦቻቸውን በተመለከተ ከመጻሕፍት መረጃ መሰብሰብ<br>• አጫጭር ዓ/ነገሮችንና አንቀጾችን ወደ ሌላ ቋንቋ መመለስ<br>• ምሳሌአዊ አነጋገሮች ሊገኙ ብት የሚችል አውድ በመፍጠር አጭር ጽሑፍ መፃፍ | |

**ግምገማ**

- ስለቋንቋ ምንነት አገልግሎትና መሠረ ዊ ጠባዮች ሀሣብ መሠንዘራቸውን መከ ተል፤
- የኢትዮጵያ ቋንቋዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ዋቢ መጻሕፍት በመጠቀም ዘርዝረው ማቅረባቸውን ማየት፤
- የቀረበላቸውን ቃል በሥነ-ድምፃዊና በቀለማዊ አፃፃፍ ዘዴ በትክክል መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤
- ከምንባቡና ከምንባቡ ውጭ ለቀረቡላቸው ቃላት ቀጥተኛ /መዝገበ-ቃላዊ/ ፍች መስጠ ቸውን መፈተሽ፤
- ከመቅረጸ-ድምፅና ከመገናኛ ብዙ ን የተላለፈን ፍሬ-ሃሣብ ሰብስበው በማምጣት ክፍል ውስጥ ማንበባቸውን መከ ተል፤
- የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለየብሔረሰቦቻቸው ያላቸውን ፋይዳ አስመልክቶ የሚያቀርቡትን ዋና ዋና ነጥብ የያዘ ንግግር መገምገም፤
- አጫጭር ዓ/ነገሮችንና አንቀጾችን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ መተርጐማቸውን መፈተሽ፤
- ምሳሌአዊ አነጋገር የሚገኝበት አውድ ፈጥረው የጻፋትን ጽሑፍ ማንበባቸውን መከ ተል፡፡

**ምዕራፍ:- ሁለት፤ ቋንቋና ህብረተሰብ** *(ክፍለ ጊዜ 12)*

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት:-*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ:- የአማርኛ ቋንቋን አጀማመርና ዕድገት ይገልፃሉ፤ የመርጃ መፃሕፍትን ተጠቅመው ሃሣብ ይወስዳሉ፤ ቃላትን በሥነ-ልሣናዊና ቀለማዊ አፃፃፍ ዘዴ ይጽፋሉ፤ ከሥርወ ቃሎች ስሞችንና ቅጽሎችን ይመሠር ሉ፤ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤ የዐ/ነገርን አይነቶችና ስልቶች ይለያሉ፤ ስላዳመጡት ነገር አስተያየት ይሰጣሉ፤ የድርሰት አፃፃፍ ሥርአትን ጠብቀው ድርሰት ይጽፋሉ፤ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በድርሰት ውስጥ ይጠቀማሉ።

| የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ | ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/ | የክሂሎት ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ |
|---|---|---|---|
| ቋንቋና ህብረተሰብ | • አንብቦ መረዳት<br>• የአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት<br>• ድምፀ-ልሣናዊ አፃፃፍ<br>• ቀለማዊ አፃፃፍ<br>• ከሥርወ-ቃል ሰምና ቅጽል መመስረት<br>• ቀጥተኛ /መዝገበ ቃላዊ/ ፍቺ<br>• የዐ/ነገር አይነቶችና ስልቶች<br>• ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች<br>• ከመፃሕፍት ሐሳብ ማግኘት<br>• ድርሰት መፃፍ<br>• ፈሊጣዊ አነጋገር | • አንብበው የተረዱትን በጽሑፍና በቃል መግለጽ<br>• የአማርኛ ቋንቋ አጀማመርንና ዛሬ የደረሰበትን ዕድገት መግለጽ<br>• አንድ ቃል በውስጡ የያዛቸውን ድምጾች በሥነ ልሣናዊ አፃፃፍ ዘዴ ማቅረብ<br>• ቃሉ የተፈጠረባቸው ተነባቢና አናባቢ ድምጾችን ያቀናጁ ቀለም መመሥረት<br>• ሥርወ ቃልን በመጠቀም ስምና ቅጽልን መመሥረት<br>• ለቃላት ቀጥተኛ / መዝገበ ቃላዊ/ ፍቺ መስጠት<br>• የዐ/ነገር አይነቶችንና ስልቶችን መለየት<br>• ከመገናኛ ብዙ ን የሚተላለፈው ልዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን ዳምጠው ጠቃሚ ሃሣብ መውሰድ<br>• ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት መረጃ ለማግኘት ልዩ ልዩ መፃሕፍትን አንብበው ሃሣብ መውሰድ<br>• የድርሰት ሥርአትን በማሟላት ድርሰት መፃፍ<br>• በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን መጠቀም | • ያንብቦ መረዳት የማስተማር ዘዴን /ቅድመ-ንባብ፣ ንባብ ጊዜና ድህረ-ንባብ ሂደቶችን/ በተግባር ላይ ማዋል<br>• ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት የሚገልጹ ልዩ ልዩ መፃሕፍትን አንብበው ሃሣብ ንዲወስዱና ክፍል ውስጥ ንዲያነቡ ማድረግ<br>• የተሰጧቸውን ቃላት በሥነ ድምፃዊ አፃፃፍ ዘዴ ንዲጽፉ ማገዝ<br>• በሥነ ድምፃዊ አፃፃፍ የቀረቡትን በቀለም አመሠራረት ያቀናጁ ንዲያቀርቡ ምሳሌ በመስጠት ማሠራት<br>• ልዩ ልዩ ሥርወ-ቃሎችን በመስጠት የተለያዩ ስሞችንና ቅጽሎችን ንዲመሠርቱ መገፋፋት<br>• መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ቀጥተኛ ፍች ንዲሰጡ ማበረ ት<br>• የተለያዩ ዐ/ነገሮችን ሰጥቶ በአይነ ቸውና በስል ቸው ንዲመድቡ ማድረግ<br>• ከመገናኛ ብዙ ን የሚተላለፉ ልዩ ልዩ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን አዳምጠው በክፍል ውስጥ አስተያየት ንዲሰጡ ማድረግ<br>• የድርሰት አፃፃፍ ሥርአትን ተከትለው ድርሰት ንዲጽፉ ማገዝ<br>• በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ንዲጠቀሙ ማበረ ት |

**ግምገማ**

- የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው መረዳ ቸውን ማረጋገጥ፤
- የሃሣብ ማግኛ መጻሕፍትን በመጠቀም ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ድገት የተሟላ ሃሣብ ይዘው በንባብ መልክ ክፍል ውስጥ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ፤
- ለቃላት መዝገበ-ቃላዊ ፍች መስጠ ቸውን ማየት፤
- ዐ/ነገሮችን በአይነትና በስል ቸው ለይተው መመደባቸውን ማየት፤
- የተሰጧቸውን ቃላት በሥነ-ልሣናዊ አፃፃፍ ዘዴ መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤
- በሥነ-ልሣናዊ አፃፃፍ ዘዴ የቀረቡትን በቀለማዊ አፃፃፍ ዘዴ ማቅረባቸውን መገምገም፤
- በተሰጧቸው ሥርወ ቃላት የተለያዩ ስሞችንና ቅጽሎችን መመሥረ ቸውን መፈተሽ፤
- ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን መሠረት አድርገው አስተያየት መስጠ ቸውን መከ ተል፤
- አንድ ሃሣብ በ ውነ ና በግል አስተያየት ላይ የተመሠረተ መሆኑን በትክክል መለየ ቸውን ማረጋገጥ፤
- በቋንቋ አጀማመርና ዕድገት ላይ ሥርአት ጠብቀው መወያየ ቸውን ማየት፤
- የድርሰት ሥርአትን ተከትለው ድርሰት መፃፋቸውን መፈተሽ፤
- በፃፉት ድርሰት ውስጥ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን መጠቀማቸውን ማየት::

**ምዕራፍ:- ሦስት፤ ሂስ** (*ክፍለ ጊዜ 12*)

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡-*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡- ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤ የሂስን ምንነት ይገልፃሉ፤ በሚሰጧቸው ርዕሶች ላይ ይከራከራሉ፤ ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን ከመገናኛ ብዙሃን ያዳምጣሉ፤ በሂሳዊ የአነባበብ ስልትም ያነባሉ፤ ይገመግማሉ፤ ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ፤ የአንድን ሃሣብ ውነ ና የግል አስተያየት ለይተው ይናገራሉ፤ ማስ ወሻ ይወስዳሉ፤ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ያስተካክላሉ።

| *የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ* | *ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/* | *የክሂሎት ብቃት* | *የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ* |
|---|---|---|---|
| *ሂስ* | • አንብቦ መረዳት<br>• ሂስ<br>• ሰዋስዋዊ ስሕተት<br>• አገባባዊ ፍች<br>• ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን ማዳመጥ<br>• ውነ ና የግል አስተያየት<br>• ክርክር<br>• ሂሳዊ ንባብ<br>• ማስ ወሻ መውሰድ<br>• ግምገማ | • አንብበው የተረዱትን በጽሑፍና በቃል መግለጽ<br>• የሂስን ምንነት መግለጽ<br>• የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን<br>• ከመገናኛ ብዙሃን ማዳመጥ<br>• በሂሳዊ የአነባበብ ስልት ማንበብ<br>• ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት<br>• የቀረቡ ሃሣቦች ዕውነ ና የግል አስተያየት መሆናቸውን ለይቶ መናገር<br>• የሂሳዊ ንባብ የአነባበብ ዘዴን ተጠቅሞ የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን መገምገምና ማስ ወሻ መውሰድ<br>• መመሪያዎችን ተከትሎ ክርክር ማካሄድ<br>• በቁጥር፣ በጾ ፣ በመደብ፣ በሐረግ አለመዛመድና በግስ አለመስማማት . . . የተዛቡ ዐ/ነገሮችን ለይቶ ማስተካከል | • ያንብቦ መረዳት የማስተማር ዘዴን /ቅድመ-ንባብ፣ ንባብ ጊዜና ድህረ-ንባብ ሂደቶችን/ በተግባር ላይ ማዋል<br>• የሂስን ምንነት ንዲገልጹ ማድረግ<br>• የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን በሂሳዊ የአነባበብ ስልት ንዲያነቡና ከመገናኛና ብዙ ንም ንዲያዳምጡ በማበረ ት ባነበቡትና ባዳመጡት ላይ በክፍል ውስጥ አስተያየት ንዲሰጡ መገፋፋት<br>• ለቃላት አገባባዊ ፍች ሰጥተው ከአገባባቸው ወጭ ደግሞ በዓ/ነገር ውስጥ ንዲጠቀሙባቸው ማገዝ<br>• ልዩ ልዩ ሃሣብ የያዙ ዓ/ነገሮችን በመስጠት ዐ/ነገሮቹ የያዙት ሃሣብ ውነ ና የግል አስተየየት መሆናቸውን በምክንያት ያስደገፉ ንዲገልጹ በማድረግ ማሠራት<br>• ልዩ ልዩ አጫጭር የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን በመስጠት በሂሳዊ የአነባበብ ስልት አንብበው በመገምገም ማስ ወሻ ንዲወስዱና ንዲወያዩ ማበረ ት<br>• በተሰጧቸው ርዕሶች ላይ መመሪያዎችን ተከትለው ክርክር ንዲያደርጉ ሁኔ ዎችን ማመቻቸት<br>• በቁጥር፣ በጾ ፣ በመደብ፣ በሐረግ አለመዛመድና በግስ አለመስማማት ... የተዛቡ ዐ/ነገሮችን በመሰጠት ንዲያስተካከሉ ማድረግ |

***ግምገማ***

- የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው መረዳ ቸውን መከ ተል፤
- የሂስን ምንነት መግለፃቸውን መከ ተል፤
- የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን ከመገናኛ ብዙ ን ማዳመጣቸውንና በሂሳዊ ንባብ ስልት ማንበባቸውን በልዩ ልዩ መመዘኛዎች መገምገም፤
- ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠ ቸውንና ከአገባባቸውም ውጭ በዓ/ነገር መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፤
- የተሰጧቸው ልዩ ልዩ ዐ/ነገሮች የያዙት ሃሣብ ውነ ና የግል አስተያየት መሆናቸውን ሲለዩ ማየት፤
- የቀረቡላቸውን አጫጭር የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች በሂሳዊ ንባብ አንብበው በመገምገም ማስ ወሻ መውሰዳቸውን መከ ተል፤
- በተሰጧቸው ርዕሶች ላይ መመሪያዎችን ተከትለው መከራከራቸውን መገምገም፤
- በቁጥር፣ በጾ ፣ በመደብ፣ በሐረግ አለመዛመድና በግስ አለመስማማት የተዛቡ ዐ/ነገሮችን ማስተካከላቸውን መከ ተል።

**ምዕራፍ:-አራት፣ ሥነ-ጽሑፍ** (*ክፍለ ጊዜ 9*)

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት:-*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ:- ለቃላት አውዳዊ፣ ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤ ልዩ ልዩ ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራዎችን በተለይም ቃለ ተውኔትን ያዳምጣሉ፤ የቀረቡ ሐሳቦችን በራሳቸው አባባል አብራርተው ይናገራሉ፤ ሥነ ጽሑፎችን በሒሳዊ ንባብ ስልት ያነባሉ፤ የኢልቦለድን ምንነትና ባሕርይ ይገልፃሉ፤ በልቦለድና በኢልቦለድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ያስረዳሉ፤ አጭር ልቦለድ ይፅፋሉ::

| *የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ* | *ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/* | *የክሂሎት ብቃት* | *የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ* |
|---|---|---|---|
| ሥነ-ጽሑፍ | • የቃላት አውዳዊ ፍች<br>• የቃላት ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች<br>• ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራዎችንና ቃለ-ተውኔቶችን ማዳመጥ<br>• ሃሣብን በራስ አባባል ማብራራት<br>• ሂሳዊ ንባብ<br>• ኢልቦለድ<br>• በልቦለድና ኢልቦለድ መካከል ያለ አንድነትና ልዩነት<br>• አጭር ልቦለድ | • ሥነ-ጽሑፍን አስመልክቶ ሐሳብ መስጠት<br>• ቃላት በዐ/ነገር ውስጥ የያዙትን ፍቺ መግለጽ<br>• የቃላትን ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠት<br>• ልዩ ልዩ ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራዎችን በተለይም ቃለ ተውኔትን ከቴፕና ልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሃንን ማዳመጥ<br>• ከንግግር ያዳመጡትን ወይም ከንባብ ያገኙትን ሐሳብ በራስ አባባል አብራርቶ ማቅረብ<br>• የተሰጠውን የሥነ ጽሑፍ ሥራ በሂሳዊ ንባብ ስልት ማንበብ<br>• የኢልቦለድን ምንነት አብራርቶ መግለጽ<br>• በልቦለድና በኢልቦለድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ማብራራት<br>• አጭር ልቦለድ መፃፍ | • ሥነጽሑፍን አስመልክቶ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገልፁ ማበረ ት<br>• ቃለ-ተውኔትን በቴፕ ቀርጾ ንዲያዳምጡ ማድረግ፣ ሌሎች የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችንም ከመገናኛ ብዙሃን ንዲከ ተሉና ያደነቋቸውንም ሥራዎች በተመለከተ ክፍል ውስጥ ሃሣብ ንዲሰጡ ማበረ ት<br>• ከቴፕ ያዳመጡትን ወይም ከመገናኛ ብዙሃን የተከ ተሉትን ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ በክፍል ውስጥ ንዲያብራሩ ማገዝ<br>• የሂሳዊ ንባብን ምንነት ተረድተው፣ አንድን አጭር ልቦለድ ንዲያነቡና ሂስ ንዲያቀርቡ ማበረ ት<br>• የኢልቦለድን ምንነት አብራርተው ንዲገልጹ ማድረግ<br>• የልቦለድንና ኢልቦለድን አንድነትና ልዩነት አብራርተው ንዲገልፁ ተገቢውን ገዛ ማድረግ<br>• ካነበቡት ምንባብ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ንዲሰጡ ቃላትን ከ ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺያቸው ጋር ንዲያዛምዱ በማድረግ ማለማመድ<br>• አንድን አጭር ልቦለድ አንብበው በውስጡ የሚገኙ የልቦለድ አላባውያኑን ገልፀው ጠንካራና ደካማ ጉኑን ንዲተቹ ማበረ ት<br>• በመረጡት ርዕስ አጭር ልቦለድ ንዲጽፉ ማገዝ |

***ግምገማ***

- ሥነ-ጽሑፍን አስመልክቶ የሚያወቁትን ሲገልፁ መከ  ተል፤
- ለቃላት አውዳዊ፣  ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠ  ቸውን ማረጋገጥ፤
- ቃለ-ተውኔቶችንና ሌሎች ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራዎችን አዳምጠው በራሳቸው አባባል ማቅረባቸውን መከ  ተል፤
- የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን በሂሳዊ ንባብ ስልት አንብበው ሂሰ መሰጠ  ቸውን ማረጋገጥ፤
- የኢልቦለድን ምንነት መግለፃቸውን መከ  ተል፤
- በልቦለድና በኢልቦለድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በትክክል ማብራራ  ቸውን መከ  ተል፤
- አጭር ልቦለድ መፃፋቸውን ማረጋገጥ፡፡

**ምዕራፍ፡- አምስት፤ ሰብአዊነት** (*ክፍለ ጊዜ 6*)

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡-*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡- የቃላትን ተመሣሣይና ተቃራኒ ፍች ይለያሉ፤ ሰዋስዋዊ ስሕተትን ያስተካክላሉ፤ ወቅ ዊና ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮችን አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፤ የአንድን ሃሣብ ዋና ዋና ነጥቦች በንግግር ያቀርባሉ፤ጭውውት ያደርጋሉ፤ በቃለ መጠይቅ ሃሣቦችን ይሰበስባሉ። ከዕለት ዕለት የሕይወት ገጠመኛቸው ማስ ወሻ ይወስዳሉ፤ ከአንድ ቋንቋ ወደ ለላ ቋንቋ ይተረጉማሉ።

| *የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ* | *ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/* | *የክሂሎት ብቃት* | *የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ* |
|---|---|---|---|
| ሰብአዊነት | • አንብቦ መረዳት<br>• ተመሣሣይና ተቃራኒ<br>• ሰዋስዋዊ ስሕተት<br>• ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ማዳመጥ<br>• በጽሑፍ ያዘጋጁትን ዋና ዋና ነጥቦች በንግግር ማቅረብ<br>• ጭውውት<br>• ቃለ-መጠይቅ<br>• የዕለት ተዕለት ማስ ወሻ መውሰድ<br>• ትርጉም | • አንብበው የተረዱትን በቃልና በጽሑፍ መግለጽ<br>• በተለያዩ ሰብአዊ ተግባራት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ድርጅቶችንና ተግባራቸውን በዝርዝር መግለጽ<br>• ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት<br>• በአንቀፅ ውስጥ የሚገኙ ሰዋስዋዊ ስሕተቶችን ማስተካከል<br>• ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ካዳመጡ በኋላ ባዳመጡት ዙሪያ ስለአቀራረቡ፣ ስለሳቢነቱ፣ መል ክት በተገቢው ሁኔ ስለማስተላለፉ አስተያየት መስጠት<br>• በቂ ዝግጅትና ልምምድ በማድረግ በፅሑፍ ያዘጋጁትን ሃሣብ ዋና ዋና ነጥቦች በንግግር ማቅረብ<br>• የምንባቡን ሃሣብ መነሻ በማድረግ ወይም በሌላ ጉዳይ ዙሪያ የራሣቸውን ጭውውት በማዘጋጀት ማቅረብ<br>• ከቃለ-መጠይቅ የሚያገ ቸውን መረጃዎች በሥርአት በማደራጀት | • ያንብቦ መረዳት የማስተማር ዘዴን /ቅድመ-ንባብ፣ ንባብ ጊዜና ድህረ-ንባብ ሂደቶችን/ በተግባር ላይ ማዋል<br>• በተለያዩ ሰብአዊ ተግባራት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ድርጅቶችንና የሚሠጧቸውን አገልግሎቶች ንዲገልፁ ማበረ ት **ለምሳሌ፡-** ቀይ መስቀል፣ ወላጅ አልባ ሕፃናት መርጃ፣ የአረጋዊያን መርጃ፣ በተለያየ የልማት ሥራ የተሰማሩ፣ የሴቶች ጥቃት ተከላካይ፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ተከላካይ . . .<br>• ከምንባቡ ለወጡ ወይም ከምንባቡ ውጭ ለተገኙ ቃላት ተመሣሣይና ተቃራኒ ቃላትን በማዛመድ ፍቻቸውን ንዲሠሩ ማድረግ<br>• አንድ አነስተኛ አንቀፅ ሰብአዊነትን የተመለከተ ወይም የሥነ-ፅሑፍ ቅንጫቢ በመውሰድ በአንቀጹ ውስጥ የሚ ዩ ሰዋስዋዊ ስሕተቶችን ንዲያስተካክሉ ማበረ ት<br>• ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን /ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥን፣ ተቀርፀው ከተቀመጡ ካሴቶች፣ ከሚነበቡ ከተለያዩ ፅሁፎች . . ./ አዳምጠው ባዳመጡት ዙሪያ አቀራረቡ፣ ሳቢነቱ፣ ና መል ክቱ በተገቢው ሁኔ መተላለፉን በቡድን ተወያይተው አስተያየት ንዲሰጡ ሁኔ ዎችን ማመቻቸት<br>• ባካባቢያቸው የሚገኙ ሰብአዊ ድርጅቶችን ንቅስቃሴ በመመልከት የተመለከቱትን በፅሁፍ ካዘጋጁ በኋላ ሃሣቡን አብላልተውና በቂ ዝግጅት አድርገው በዋና ዋና ነጥቦች ዙሪያ ንግግር ንዲያደርጉ መገፋፋት<br>• ጭውውት መል ክት ለማስተላለፍ ያለውን ጠቀሜ ካለፈው ትምህርት በማስ ወስ በመረጧቸው ርዕሶች ላይ /ኤድስ፣ ልማት፣ ሰብአዊ ተግባር፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ . . ./ የራሳቸውን ጭውውት በማዘጋጀት ክፍል ውስጥ ንዲያቀርቡ ሁኔ ዎችን |

| *የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ* | *ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/* | *የክሂሎት ብቃት* | *የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ* |
|---|---|---|---|
| | | በፅሑፋቸውና በንግግራቸው መጠቀም<br>• የዕለት ተዕለት የሕይወት<br>• ገጠመኞቻቸውን በማስ ወሻ መያዝ<br>• ከአንድ ቋንቂ ወደሌላ ቋንቋ መተርጐም | ማመቻቸት<br>• በግል፤በጥንድና በቡድን ቃለ-መጠይቅ አዘጋጅተው በክፍል ውስጥ ና ከክፍል ውጭ ቃለ-መጠይቅ አካሂደው መረጃ<br>• ንዲሰበስቡ፣ መረጃዎችን በሥርአት ንዲያደራጁና<br>• በጽሑፍም ሆነ በንግግር ንዲያቀርቡ ማለማመድ<br>• ቀደም ብለው በተማሩት የማስ ወሻ አያያዝ ዘዴ በመጠቀም የዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞቻቸውን<br>• በማስ ወሻ ንዲይዙ ማድረግ<br>• ከአንድ ድርሰት አነስተኛ ቅንጫቢ በአንቀፅ መልክ በመውሰድ ትምህርት ወደሚሰጥባቸው ሃገራዊ ቋንቋዎች ካላመቸም ወደ ንግሊዝኛ ቋንቋ ንዲተረጉሙ ማበረ ት |

***ግምገማ***

- ያነበቡትን ጽሑፍ መረዳ ቸውን ማረጋገጥ፤
- በተለያዩ ሰብአዊ ተግባራት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ድርጅቶችንና የሚሰጧቸውን ግልጋሎት ሲገልፁ መከ ተል፤
- የቃላትን ተመሣሣይና ተቃራኒ ፍቺ በትክክል መዛመዳቸውን ማየት፤
- የአንቀጽን ሰዋስዋዊ ስሕተት ለይተው ማስተካከላቸውን ማየት፤
- በወቅ ዊና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ባዳመጡት ዙሪያ ስለአቀራረቡ፣ ስለሣቢነቱ፣ መል ክት በተገቢው ሁኔ ስለማስተላለፉ አስተያየት ሲሰጡ መከ ተል፤
- ባዘጋጁት ጽሑፍ ዋና ዋና ነጥቦች ዙሪያ የሚያቀርቡትን ንግግር መከ ተል፤
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ክፍል ውስጥ የሚቀርበውን ጭውውት መከ ተል፤
- ከቃለ መጠይቅ የሰበሰቡትን መረጃ በሥርአት አደራጅተው በጽሑፍና በንግግር ማቅረባቸውን መገምገም፤
- የዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞቻቸውን በማስ ወሻ መያዛቸውን ማየት፤
- በአንቀፅ መልክ የቀረበውን ፅሁፍ ከመገኛ ቋንቋው ወደሌላ ቋንቋ መተርጐማቸውን መፈተሽ።

# የሁለተኛው ወሰነ-ትምህርት

**ምዕራፍ:- ስድስት፤** (*ክፍለ ጊዜ 15*)

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት:-*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ:- ለቀረቡላቸው ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ይሰጣሉ፤ ስርአተ-ነጥቦችን በተለይም ማለበሚያን/አስተሪክስ/ በአግባቡ በፅሑፋቸው ውስጥ ይጠቀማሉ፤ የሳይንሳዊ ግኝቶችንና የምርምር ወጤቶችን አዳምጠው ያገኙትን ሐሣብ ይፅፋሉ፤ ያነባሉ፤ ዕውነ ና የግል አስተያየትን ይለያሉ፤ የጥና ዊ ጽሑፍ መመሪያ ተከትለው ጥና ዊ ጽሑፍ ይጽፋሉ፤ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገ ቸውን ሐሣቦች ይሰበስባሉ፤ ያደራጃሉ፤ ሐሣቦቹን በግሉ-ገለፃና በጭምቀ ሐሣብ ይገልፃሉ፤ የመረጃ ምንጭ አፃፃፍ ስርአትን በመከተል የተጠቀሙባቸውን የመረጃ ምንጮች ይፅፋሉ::

| *የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ* | *ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/* | *የክሂሎት ብቃት* | *የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ* |
|---|---|---|---|
| *ጥና ዊ ፅሑፍ* | • አንብቦ መረዳት<br>• ቀጥተኛ ፍቺ<br>• ሥርዓተ-ነጥቦች ማለበሚያ/አስትሪክስ/<br>• ከመገናኛ ብዙሃን ሳይንሳዊ ግኝቶችንና፣ የምርምር ውጤቶችን ማዳመጥ<br>• ዕውነ ና የግል አስተያየት<br>• ልዩ ልዩ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ መመሪያዎችን መከተልና ጽሑፍን ማዘጋጀት<br>• ከመጻሕፍት፣ ከሰንጠረዥ፣ ከመጠይቅና ከቃለ-መጠይቅ ሃሣቦችን ማግኘት<br>• ሃሣቦችን በግሉ-ገለፃና በጭምቀ ሃሣብ ማቅረብ<br>• የመረጃ ምንጮች አፃፃፍ<br>• ጥና ዊ ጽሑፍ | • አንብበው የተረዱትን በቃልና በጽሑፍ መግለጽ<br>• ለቃላት ቀጥተኛ /መዝገበ ቃላዊ/ ፍቻቸውን መፈለግ<br>• ስርአተ ነጥቦችን ንደአገባባቸው፣ በተለይም ማለበሚያን /አስትሪክስ/ መጠቀም<br>• ከመገናኛ ብዙሃን የሚያዳምጧቸውን የሳይንሳዊ ግኝቶችንና የምርምር ውጤቶችን ባጭሩ ጽፎ ማንበብ<br>• ከጥና ዊ ፅሑፎች ውስጥ ውነ ና የግል አስተያየትን መለየት<br>• ጥና ዊ ፅሑፍ ለመፃፍ የአሠራር መመሪያዎችን በመከተል ጽሑፍን ማዘጋጀት<br>• ለጥና ዊ ፅሑፋቸው ከመፃሕፍት፣ ከሰንጠረዥ፣ ከመጠይቅና ከቃለ-መጠይቅ ሃሣብ መሰብሰብ<br>• ከመረጃ ምንጮች ያገ ቸውን ሃሣቦች በግሉ-ገለፃና ጭምቀ-ሃሣብ መግለፅ<br>• ለጥና ዊ ፅሑፍ መረጃ ምንጮችን መፃፍ<br>• ጥና ዊ ጽሑፍ ማዘጋጀት | • ያንብቦ መረዳት የማስተማር ዘዴን /ቅድመ-ንባብ፣ ንባብ ጊዜና ድህረ-ንባብ ሂደቶችን/ በተግባር ላይ ማዋል<br>• ለቀረቡላቸው ቃላት መዝገበ-ቃላትን ተጠቅመው ፍቺ ንዲፈልጉ ማድረግ<br>• ባለፉት የክፍል ደረጃዎች የተማሯቸውን ሥርአተ-ነጥቦችን በመከለስና በማለበሚያ /አስትሪክስ/ ላይ አጽንኦት ሰጥቶ አጠቃቀሙን በማሳየት ንዲጠቀሙበት ማገዝ<br>• ከመገናኛ ብዙሃን ያዳመጧቸውን የምርምር ወጤቶችና የሳይንስ ግኝቶችን ባጭሩ ፅፈው ክፍል ውስጥ ንዲያነቡ ማበረ ት<br>• በምሳሌነት ከቀረበላቸው የጥናት ፅሑፍ ውስጥ ዕውነ ና የግል አስተያየት የሆነኑትን ሐሳቦች ለይተው በማውጣት በመረጃ አስደግፈው ንዲያብራሩ ማበረ ት<br>• የፕሮጀክት ዘዴን በመጠቀም በቡድን ሆነው ጥና ዊ ጽሑፍ ለመጻፍ የሚያስችላቸውን መመሪያ በመከተል ንዲጽፉ ማገዝ<br>• ለጥና ዊ ፅሑፋቸው ከመፃሕፍት፣ ከመጠይቅ፣ ከቃለ-መጠይቅ. . . የሰበሰቧቸውን ሃሣቦች በግሉ-ገለፃና ጭምቀ-ሃሣብ ንዲገልፁ ማገዝ<br>• ሃሳብ ያገኙባቸውን የመረጃ ምንጮች ስርአት ጠብቀው ንዲፅፉ ማድረግ |

***ግምገማ***

- የቀረበውን ጥና ዊ ጽሑፍ አንብበው መረዳ ቸውን ማረጋገጥ፤
- ለቃላት ቀጥተኛ /መዝገበ-ቃላዊ/ ፍቺ መስጠ ቸውን ማረጋገጥ፤
- ስርአተ-ነጥቦችን በተለይም የማለበሚያን /አስትሪክስ/ አገባብና አጠቃቀም ተገንዝበው በፅሑፋቸው ውስጥ መጠቀማቸውን ማየት፤
- ከመገናኛ ብዙሃን ያዳመጧቸውን የምርምር ወጤቶችና ሳይንሳዊ ግኝቶች ፅፈው ማንበባቸውን ማየት፤
- ዕውነ ና የግል አስተያየትን ለይተው በማስረጃ በማስደገፍ መግለፃቸውን መከ ተል፤
- ጥና ዊ ፅሑፍ ለማዘጋጀት የሚያስችሏቸውን መመሪያዎች ተከትለው ጥና ዊ ፅሑፍ መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤
- በጥና ዊ ፅሑፋቸው ሃሣባቸውን በግል-ገለፃና በጭምቀ ሐሣብ መግለፃቸውን ማየት፤
- ሃሣብ ለማግኘት የመረጃ ምንጮችን መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፤
- የመረጃ ምንጮችን የአፃፃፍ ስርአት ጠብቀው መፃፋቸውን ማየት።

**ምዕራፍ፡- ሰባት፤ ሥነ ግጥም** *(ክፍለ ጊዜ 15)*

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡-*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡- በግጥም ውስጥ የቃላትን አገባባዊ፣ ዕማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይለያሉ፣ በድምጾች መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር የሚመጡ የትርጉም ለውጦችን ያሣያሉ፤ መገናኛ ብዙሃንን ይከ ተላሉ፤ የግጥሞችን መል ክት በራሳቸው አባባል ይተነትናሉ፤ የዘይቤዎቹን ምንነት ይገልፃሉ፤ በግጥም ውስጥ የዘይቤዎችን አጠቃቀም ይለያሉ፤ ግጥም ይፅፋሉ፤ ቅኔን ይፈ ሉ፡፡

| *የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ* | *ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/* | *የክሂሎት ብቃት* | *የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ* |
|---|---|---|---|
| ሥነ ግጥም | • ግጥምን አንብቦ መረዳት<br>• የቃላት አገባባዊ፣ ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ<br>• በቃላት ውስጥ ድምጾች በመጥበቅና በመላላት፣ በመርዘምና በማጠር የሚያመጡት የትርጉም ለውጥ የአማርኛ ቋንቋ የማይመለከ ቸውን ማስቀረት<br>• ከመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ልዩ ልዩ የሥነ-ፅሑፍ ሥራዎችን፣ ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን መከ ተል<br>• አንድን ሃሣብ በራስ አባባል ማቅረብ<br>• ከግጥም መፃሕፍት ሃሣብ ማግኘት<br>• ዘይቤ /ገድሎ ማዳን፣ንቡር ጠቃሽ /<br>• ዘይቤያዊ አጠቃቀም በሥነ ግጥም ውስጥ /ሰውኛ፣ ምፀትና ተምሣሌት/<br>• ግጥም መፃፍ<br>• ቅኔ /ኀብረ ቃል፣ የቅኔ ሰምና ወርቅ/ | • ግጥምን አንብቦ መል ክቱን በቃልና በጽሑፍ መግለጽ<br>• በግጥም ውስጥ ቃላት የሚኖራቸውን አገባባዊ ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መለየት<br>• ከግጥም ከወጡ ቃላት በድምጾች መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር የሚከሰቱ የትርጉም ለውጦችን ማሳየት<br>• በመገናኛ ብዙሃን በግጥም የሚተላለፉ ልዩ ልዩ የሥነ-ፅሑፍ ሥራዎችን፣ ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ተከ ትሎ መግለፅ<br>• የንቡር ጠቃሽና ገድሎ ማዳን ዘይቤዎችን ምንነት ማብራራት<br>• በግጥም የቀረቡ ሃሣቦችን በራሣቸው አባባል መግለፅ<br>• ከግጥም መፃሕፍት የተገኙ ሃሣቦችን ከግጥሙ ቅርፅና ይዘት አኳያ መግለጽና መተንተን<br>• በሥነ ግጥም ውስጥ የሰውኛ ፣ የምፀትና የተምሣሌት ዘይቤዎችን አጠቃቀም መለየት<br>• በተለያዩ ር ሶች ልዩ ልዩ | • በግጥም ውስጥ የቃላትን አገባባዊ፣ ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺያቸውን ጠንቅቀው ንዲገነዘቡ የተለያዩ ምሣሌዎችን በመስጠት ማለማመድ<br>• በቡድን ሆነው ግጥምን ደጋግመው በማንበብ የድምጾች መጥበቅና መላላት መርዘምና ማጠር የሚያመጣውን የቃላት ትርጉም ለውጥ ንዲለዩ ማድረግ<br>• በመገናኛ ብዙሃን በግጥም የሚተላለፉ ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን፣ ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ተከ ትለው ያገኙትን ከቅርፅና ይዘት አኳያ ንዲገልጹና ንዲተነትኑ መርዳት<br>• የተለያዩ ግጥሞችን በማቅረብ በግጥሙ ውስጥ የሰውኛ፣ የምፀትና የተምሣሌት ዘይቤዎችን አጠቃቀም ንዲለዩ ማበረ ት<br>• በተለያዩ ርዕሶች ልዩ ልዩ ዘይቤዎችን ተጠቅመው ግጥም ንዲፅፉና ክፍል ውስጥ ንዲያነቡ ማገዝ<br>• በቅኔ ህብረቃሎች ውስጥ ያሉ ድምጾች ጠብቀውና ላልተው፣ ረዝመውና አጥረው ሲነበቡ የሚያመጡትን የፍቺ ለውጥ ጠንቅቀው ንዲገነዘቡና ለቅኔዎች ፍቺ ንዲሰጡ ማበረ ት<br>• የገድሎ ማዳንና ንቡር ጠቃሽ ዘይቤዎችን ምንነት ንዲለዩ ምሳሌ በማስደገፍ ማስረዳት |

| የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ | ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/ | የክሂሎት ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ |
|---|---|---|---|
| | | ዘይቤዎችን ተጠቅመው ግጥም መፃፍ<br>• በቅኔ ህብረ-ቃሎች ውስጥ ባሉ ድምጾች መጥበቅና መላላት መርዘምና ማጠር ምክንያት የሚመጡ የፍቺ ለውጦችን መግለጽ<br>• ለቅኔ ፍቺ መስጠት | |

**ግምገማ**

- የቀረበውን ግጥም አንብበው መል ክቱን መረዳ ቸውን መከ ተል፤
- በግጥም ውስጥ የቃላት አገባባዊ፣  ማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺን ጠንቅቀው መለየ ቸውን ማረጋገጥ፤
- በቃላት ውስጥ በድምጾች መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር የሚመጣውን የፍቺ ለውጥ መለየ ቸውን መከ ተል፤
- በመገናኛ ብዙሃን በግጥም የሚተላለፉ ልዩ ልዩ የሥነ ፅሑፍ ሥራዎችን፣ ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ተከ ትለው በራሣቸው አባባል ማቅረባቸውን ማየት፤
- ግጥምን ከቅርጽና ከይዘት አኳያ መግለጻቸውንና መተንተናቸውን መከ ተል፤
- በግጥም ውስጥ የሰውኛ፣ የምፀትና የተምሣሌት ዘይቤዎችን አጠቃቀም ለይተው ግጥም መፃፋቸውን መከ ተል፤
- የቅኔን ህብረ-ቃል ድምጾች ጠብቀውና ላልተው፣ ረዝመውና አጥረው ሲነበቡ የተለየ ፍቺ የሚሰጡ መሆናቸውን ተገንዝበው ሰምና ወርቅ ፍቺ መስጠ ቸውን መከ ተል።

**ምዕራፍ፡- ስምንት፤ ውሣኔ ላይ መድረስ** (*ክፍለ ጊዜ 12*)

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡-*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡- ለቃላት ቀጥተኛ፣ ተመሣሣይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤ ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚተላለፉ መል ክቶችን ከመገናኛ ብዙሃን ያዳምጣሉ፤ ሥርአትን ተከትለው ይከራከራሉ፤ መመሪያዎችን ተከትለው ሥራዎችን ይሠራሉ፤ ከቃለ መጠይቅና ከሠንጠረዥ ሃሣብ ያገኛሉ፤ ማስ ወሻ የመውሰድ ልምድ ያዳብራሉ፡፡

| የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ | ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/ | የክሂሎት ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ |
|---|---|---|---|
| ውሣኔ ላይ መድረስ | • አንብቦ መረዳት<br>• የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ<br>• የቃላት ተመሣሣይና ተቃራኒ ፍቺ<br>• ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዩች<br>• ክርክር<br>• መመሪያን መከተል<br>• መረጃን ከሠንጠረዥና ከመጠይቅ ማግኘት<br>• ማስ ወሻ መውሰድ /ከዕለት ዕለት የሕይወት ገጠመኝና ከዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን/ | • አንብበው የተረዱትን በቃልና በጽሑፍ መግለጽ<br>• ለቃላት ቀጥተኛ ፍቺ መስጠት<br>• ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት<br>• ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከመገናኛ ብዙሀን ማዳመጥና ያገኙትን ሃሣብ ማቅረብ<br>• ውሳኔ ላይ የመድረስ ችግርን አስመልክቶ ክርክር ማካሄድ<br>• መመሪያዎችን በመከተል ልዩ ልዩ ሥራዎችን ማከናወን<br>• በቃለ መጠይቅና በሠንጠረዦች አማካይነት ሃሣብ ማግኘት<br>• ከዕለት ዕለት የሕይወት ገጠመኝ፣ ከአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ማስ ወሻ መውሰድ | • ያንብቦ መረዳት የማስተማር ዘዴን /ቅድመ-ንባብ፣ ንባብ ጊዜና ድህረ-ንባብ ሂደቶችን/ በተግባር ላይ ማዋል<br>• ለቃላት ቀጥተኛ፣ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ንዲሰጡ መልመጃዎችን በማቅረብ ማሠራት<br>• ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ንዲከ ተሉና ጠቃሚ ሐሣቦችን በማስ ወሻ በመያዝ ንዲያቀርቡ ማበረ ት<br>• ብዙ ሰዎች በተለይም ወጣቶች በአንድ ጉዳይ ላይ ከውሳኔ ለመድረስ ያለባቸውን ችግር አስመልክቶ በቡድን ተከፋፍለው ክርክር ንዲያካሂዱ ማገዝ<br>• በአንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመድረስ ንደመመሪያ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሃሣቦችን ልምድ ካላቸው ሰዎች በመጠየቅና መፃሕፍት በማንበብ አሰባስበው ንዲያቀርቡና የተግባር መመሪያዎችም ንዲያደርጓቸው ማበረ ት<br>• ውሳኔ ላይ መድረስን አስመልክቶ በቃለ-መጠይቅ መልሶችና በሰንጠረዦች ካገ ቸው ሃሳቦች በመነሳት ውሳኔ ላይ ንዲደርሱ ማገዝ<br>• የዕለት ዕለት የሕይወት ገጠመኞቸውን በማስ ወሻ የመያዝ ባህል ንዲያዳብሩ፣ ከዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን የሚያገኙዋቸውን መረጃዎም መዝግበው ንዲይዙና ተጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን ለክፍል ንዲያቀርቡ ማበረ ት |

**ግምገማ**

- የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው መረዳ ቸውን ማረጋገጥ፤
- ለቃላት ቀጥተኛ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ፤
- ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከመገናኛ ብዙሃን መከ ተላቸውን በተለያዩ መንገዶች መፈተሽ፤
- ርዕሱን መሠረት አድርገው ስርአቱን በመከተል ክርክር ማድረጋቸውን መከ ተል፤
- መመሪያዎችን ተከትለው ሥራ መሥራ ቸውን ማየት፤
- ከቃለ-መጠይቅ መልሶችና ከሠንጠረዦች ሃሣብ መውሰዳቸውን መከ ተል፤
- ከዕለት ዕለት የሕይወት ገጠመኛቸውና ከዓለም አቀፍ መገናኛዎች ማስ ወሻ መውሰዳቸውን ማረጋገጥ፡፡

## ምዕራፍ:- ዘጠኝ፤ ህብረተ-ሰብና ጤና (*ክፍለ ጊዜ 12*)

***የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት:-*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ:- በሳይንሳዊ ግኝቶችና በወቅ ዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚተላለፉ መግለጫዎችንና መል ክቶችን ይገልፃሉ፤ ውነ ና የግል አስተያየትን ለይተው ይናገራሉ፤ ውይይት ያካሄዳሉ፤ ከመጻሕፍትና ከሰንጠረዥ የሰበሰቡትን ሃሣብ ይገልፃሉ፤ ከዕለት ዕለት ገጠመኛቸው ማስ ወሻ ይይዛሉ፤ ጽሑፍን አሳጥረው ይጽፋሉ፤ የትርጉም ሥራ ይሠራሉ፤ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ያብራራሉ፤ ቅኔዎችን ይፈ ሉ::

| *የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ* | *ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/* | *የክሂሎት ብቃት* | *የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ* |
|---|---|---|---|
| *ህብረተ-ሰብና ጤና* | • አዳምጦ መረዳት<br>• ሳይንሳዊ ግኝቶችን ማዳመጥ<br>• ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ማዳመጥ<br>• ውነ ና የግል አስተያየት<br>• ውይይት<br>• ከመጻሕፍትና ከሰንጠረዥ ሃሣብ ማግኘት<br>• ከዕለት ዕለት ገጠመኝ ማስ ወሻ መውሰድ<br>• ማሳጠር<br>• ሃሣብን ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጐም<br>• ምሳሌያዊ አነጋገር<br>• ፈሊጣዊ አነጋገር<br>• ቅኔን መፍ ት | • አዳምጠው የተረዱትን በቃልና በጽሑፍ መግለጽ<br>• የህብረተሰብ ጤና መጠበቅ ያለውን ፋይዳ መናገር<br>• በሳይንሳዊ ግኝቶች ዙሪያ በተለያዩ መድረኮችና መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ሃሣቦችን ማዳመጥ<br>• በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ማዳመጥ<br>• በተጠየቃዊ አስተሰሰብ ውነ ና የግል አስተያየትን ለይቶ መናገር<br>• ህብረተሰብንና ጤናን በተመለከተ ውይይት ማካሄድ<br>• ህብረተሰብና ጤናን በተመለከተ ከመጻሕፍትና ከሰንጠረዥ ሃሣብ ማግኘት<br>• ከዕለት ዕለት ገጠመኝ ማስ ወሻ መውሰድ<br>• የአንድን ጽሑፍ ሃሣብ አሳጥሮ መፃፍ<br>• ሃሣብን ከአንድ ቋንቋ ወደ ተቀባዩ ቋንቋ መተርጐም<br>• የምሳሌያዊ አነጋገሮችን መል ክት ማብራራት | • የአዳምጦ መረዳት ማስተማር ዘዴን በተግባር ላይ ማዋል<br>• የህብረተሰቡ ጤና መጠበቅ የሚኖረውን ጠቀሜ ንዲገልጹ ማገዝ<br>• በሳይንሳዊ ግኝቶች፣ በወቅ ዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ፣ በተለያዩ መድረኮችና መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ትምህር ዊ መግለጫዎችንና መል ክቶችን አዳምጠው ዋና ዋና ነጥቦችን ንዲጽፉና በክፍል ውስጥ ንዲያቀርቡ ማበረ ት<br>• ውነ ና የግል አስተያየትን ለይተው በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ንዲናገሩ ማድረግ<br>• የውይይትን ሥርአት ጠብቀው በህብረተሰብና ጤና ዙሪያ ውይይት ንዲያካሄዱ ማገዝ<br>• ህብረተሰብና ጤናን በተመለከተ ከመጻሕፍትና ከሰንጠረዥ ሃሣብ ንዲያሰባስቡና ያሰባሰቡትን ሃሣብ በጽሑፍ አደራጅተው ንዲያቀርቡ ማበረ ት<br>• ከዕለት ዕለት ገጠመኝ ማስ ወሻ መያዝ የሚኖረውን ጠቀሜ በመግለጽ የራሳቸውን ገጠመኝ በማስ ወሻ የመያዝ ልምድ ንዲያዳብሩ ማገዝ<br>• የማሳጠር መመሪያን ተከትለው የአንድን ጽሑፍ ሃሣብ አሳጥረው ንዲያቀርቡ ማድረግ<br>• የትርጉምን ጠቀሜ በማስ ወስ አጫጭር አንቀጾችን ትምህርት ወደሚሰጥባቸው ሃገራዊ ቋንቋዎች ካላመቸም ወደ ንግሊዝኛ ቋንቋ ተርጉመው ንዲያቀርቡ ማበረ ት<br>• ገንቢ ሃሣብ የሚያስተላልፉ ዐ/ነገሮችን በምሳሌ አቅርቦ ተመሳሳይ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ንዲሰበስቡና የሚያስተላልፉትን መል ክት ንዲያብራሩ ማገዝ<br>• በፈሊጣዊ አነጋገር የተነገረውን ሃሣብ በተራ አነጋገር፣ |

| የቋንቋ ማስተማሪያ አውደ-ርዕስ | ይዘት /ቋንቋ፣ ሰዋስውና ሥነፅሑፍ/ | የክሂሎት ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ |
|---|---|---|---|
| | | • የፈሊጣዊ አነጋገሮችን መል ክት መግለጽ<br>• የቅኔን ሰምና ወርቅ ለይቶ መፃፍ | በተራ አነጋገር የተነገረውን ደግሞ በፈሊጣዊ አነጋገር ንዲገልጹ በምሳሌ በማስረዳት ማለማመድ<br>ምሳሌ:- ሆደ-ሰፊ /ፈሊጣዊ አነጋገር/ ----- ጋሻ /ተራ አነጋገር/<br>ክፉ /ተራ አነጋገር/ ------- ሆደ-መጋዝ /ፈሊጣዊ/<br>• ቅኔ ውስጣዊ ስሜትን ለመግለጽ ያለውን ፋይዳ በማስ ወስ ከቅኔ ግጥም ውስጥ ህብረ-ቃሉን ንዲያወጡና ሰምና ወርቁን ለይተው ንዲጽፉ ማድረግ |

***ግምገማ***

- የቀረበውን ጽሑፍ አዳምጠው መረዳ ቸውን ማረጋገጥ፤
- የህብረተሰቡ ጤና መጠበቅ የሚኖረውን ጠቀሜ መግለፃቸውን ማረጋገጥ፤
- በሳይንሳዊ ግኝቶችና በወቅ ዊ ጉዳዮች ዙሪያ በተለያዩ መድረኮችና መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ትምህር ዊ መግለጫዎችን አዳምጠው ማስ ወሻ መያዛቸውን ማየት፤
- ውነ ንና የግል አስተያየትን ለይተው በተጠየቃዊ አስተሳሰብ መግለጻቸውን መከ ተል፤
- ሥርአትን ጠብቀው መወያየ ቸውን መከ ተል፤
- ከመጻሕፍትና ከሰንጠረዥ ሃሣብ ማሰባሰባቸውን ማየት፤
- ከዕለት ዕለት ገጠመኞቸው ማስ ወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- አንድን ጽሑፍ አሳጥረው መፃፋቸውን ማየት፤
- የትርጉም ሥራ መሥራ ቸውን መገምገም፤
- ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ሰብስበው የሚያስተላልፉትን መል ክት መግለጻቸውን መከ ተል፤
- በፈሊጣዊ አነጋገር የተነገረውን በተራ አነጋገር፣ በተራ አነጋገር የተነገረውን በፈሊጣዊ አነጋገር መግለፃቸውን ማየት፤
- የቅኔን ሰምና ወርቅ ለይተው መፃፋቸውን ማረጋገጥ::

## ለማጣቀሻነት የሚያገለግሉ መጻሕፍት ዝርዝር፡-


1. ሀዲስ አለማየሁ:: 1958 :: **ፍቅር  ስከ መቃብር::** አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::
2. ሀዲስ አለማየሁ:: 1980:: **የልምዣት::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::
3. ማህተመ ስላሴ ወ/መስቀል:: 1999:: **አማርኛ ቅኔ ከነፍቻቸው::** አዲስ አበባ:  ሌኒ ማተሚያ ቤት  ላፊነቱ የወሰነ የግል ማህበር::
4. መስፍን ሀ/ማርያም:: 1976:: **የቡና ቤት ስ ሎችና ሌሎችም ወጐች**:: አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት::
5. መንግሥቱ ለማ:: 1955:: **የግጥም ጉባኤ::** አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::
6. መኩሪያ ወርቁ:: 1982:: **ምሳሌያዊ አነጋገር::** አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::
7. ሰለሞን ሃለፎም:: 1997:: **የድርሰት አጻጻፍ::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::
8. በአሉ ግርማ:: 1962:: **ከአድማስ ባሻገር::** አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::
9. በድሉ ዋቅጅራ:: 1996:: **በስነ-ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::
10. ባዬ ይማም:: 1987:: አማርኛ ሰዋሰው:: አዲስ አበባ: ት/መ/ማ/ማ/ድ/
11. ብርሃኑ ገ/ጻድቅ:: 1993:: **አማርኛ ፈሊጣዊ አነጋገሮችና ፍቺዎቻቸው::** አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተማያ ኢንተርኘራይዝ::
12. ተሰማ ሀ/ሚካኤል:: 1951:: **ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት**:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::
13. ተክለማርያም ፋን  ዬ:: 1964:: **ሆህተ ጥበብ ዘ-ስነጽሑፍ::** አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር::
14. ደለ ገድሌ:: 1996:: **ቅኔና ቅኔያዊ ጨዋ  ለትዝ  ::** አዲስ አበባ፣ ጉተንበርግ ማተሚያ ቤት::
15. ንጉሤ ነገዎ:: 1996:: **የቅኔ አፈ  ት ዘዴዎችና የምርጥ ቅኔዎች ስብስብ**:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::
16. አለም  ሸቱ:: 1992:: **መሠረ  ዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሜያ ቤት::
17. አማረ ማሞ:: 1968:: **የልቦለድ ጽሑፍ መመሪያ::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::
18. አማረ ማሞ:: 1976:: **የቀለም ጠብ  ፣የኢ-ልቦለድ አጻጻፍ መመሪያ::** አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት::
19. አምሳሉ አክሊሉና ዳኛቸው ወርቁ:: 1979:: **የአማርኛ ፈሊጦች::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::
20. አብዱራህመቶና ሌሎችም:: 1980:: **አጫጭር ልቦለዶች::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::
21. አብዱራህመቶና ንጉሜ አየለ ተካ:: 1979:: **ሙሽራውና ሌሎች. . .** አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳ  ሚ ድርጅት::
22. ከበደ ገ/መድህን:: 1992:: **ሳይንሳዊ የቅኔ አፈ  ት ስልት::** አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት::
23. ደረጀ ገብሬ:: 1996:: **ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::
24. ደስ  ተክለወልድ:: 1962:: **አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት::** አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::
25. ደበበ ሰይፉ:: 1980:: **የብርሃን ፍቅር::** አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳ  ሚ ድርጅት::

**26.** ዳኛቸው ወርቁ:: 1985:: **የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ::** አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት::

**27.** ፀጋዬ ገ/መድህን:: 1966:: **ሳት ወይአበባ::** አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

**28.** ፍቃደ አዘዘ:: 1985:: **ጨኸት::** አዲስ አበባ፣ ት/መ/ማ/ማ/ድ/

**29.** ዘሪሁን አስፋው:: 1992:: **የስነ-ጽሑፍ መሠረ ውያን::** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::

**30.** የሻው ተሰማ::1996:: **ልሣነ ብዕር ከመ ልሣነ ሰብዕ::** አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

**31.** የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: 1982:: **የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች ::** አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

**32.** የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: 1993:: **የአማርኛ መዝገበ ቃላት::**
አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

**33.** ጌ ሁን አማረ:: 1989:: ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት

34 የግጥም መድብል:: 1977:: **ጽጌረዳ ብዕር**:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::

35 መስፍን ሀ/ማርያም:: 1983:: **አውደ-ዓመት::** አዲስ አበባ፣

36 በዓሉ ግርማ:: 1972:: **ደራሲው::** አዲስ አበባ፣

37.ተስፋዬ ሽዋዬ:: 1986:: **አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎ ን ማዳበር::** አዲስ አበባ፣

38. ተፈራወርቅ አራምዴ:: **የአማርኛ ሥነ ቃል::** አዲስ አበባ፣

39. ቴዎድሮስ ሙላቱ:: 1986:: **አውደ ጥበብ::** አዲስ አበባ፡

40. አምሳሉናደምሴ:: 1982:: **ጥሩ የአማርኛ ድርሰት ንዴት ያለ ነው?** አዲስ አበባ፣

41. ዮሐንስ አድማሱ:: 1990:: **ስኪ ተጠየቁ::** አዲስ አበባ::

**42.** ጥላሁን በየነ:: **ልሣን**::